*ከቃሊቲ ወህኒ ቤት የተላከ ደብዳቤ*

**በብርቱካን ሚደቅሳ**
**ጥር 17 ቀን 1998 ዓ.ም**

ኢህአዴግን እረፍት የነሳ መንፈስ አለ፤ የቅንጅት መንፈስ:: የነፃነትን ዳናና ፈለግ ፍለጋ የሚኳትኑ፣ በነፃነት ጥም የተቃጠሉ ያገሬ ሰዎች በዋናና በገጠር ከተሞች ከዳር እስከ ዳር በነቂስ የመነሳታቸው ሪፖርት ያለሁበትን የእስር ቤት ግርግዳ ጥሶ ከጆሮዬ ደረሰ::

በትምህርት ቤቶች እና በኮሌጆች ያሉ ታናናሽ ብላቴኖች በግልፅነትና በድፍረት፣ በልበ-ሙሉነት እና በፍፁም ቁርጠኝነት ከዕድሜያቸው በሚልቅ አስገራሚ ብስለት «ነፃነታችንን አሁን» አሉ:: ካህናቱን እግዚአብሔር እንደሚወደውና እንደ ቃሉ እንዲኖሩና እንዲያስተምሩ ወጣቶቹ ቀርበው ሲጠይቋቸው ቀሳውስቱ አንገታቸውን በሃፍረት ደፉ::

የወጣቶቹ አሰቃዮች እነዚህን ጀግኖች ፊት ለፊት ተጋፍጠው የሚሟገቱበት በቂ ድፍረት ማሰባሰብ አቃታቸው:: የወጣቶቹ አሰቃዮች መሟገት የሚችሉበት አቅምም የላቸውምና «ቅንጅት» ብለው ፈረጇቸው፤ አወገዟቸው:: የቅንጅትን መንፈስ «እንደ ጋኔል» ከወጣቶቹ ልብና አዕምሮ ለማውጣትና ለማባረር ዳከሩ::

እነዚህ ሰልፈኞች ፍቅርተኛ (Romantic) ወጣቶች ናቸው:: ወጣቶቹ በግልፅ የተቀመረ ርዕዮተ ዓለም፤ የረቀቀ ፍልስፍና ይህንን ዓለም የሚመለከቱበት አስተምህሮ ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል:: ይህ ባይሆን እንኳ ፍቅርተኛ ማንነታቸው የወጣቶቹን ሁለንተና ለነፃነት፣ ለጀብድ፣ መፃዒ ሥጋትን እና አደጋን ለመቋቋምና ለመቀበል፤ ከልባዊ ስሜት እና ሕይወትን በመስዋዕትነት አሳልፎ ለመስጠት በቁርጠኝነት የተሰለፈ ነው:: እነዚህ ሴቶችና ወንዶች ፍርሃትን አያውቁትም:: ግርፊያና እስር አይደንቃቸውም:: ለዳግማዊና ለሳልሳዊ ዙር ለሌላም ብዙ ብዙ ስቃይ ሁለንተናቸውን መልሰው መላልሰው አዘጋጅተዋል::

በጥቅምት ወር መገባደጃ የኢህአዴግ የደኅንነት ሰዎች የቅንጅትን አመራሮች ከየመኖሪያችን ነትተው ባዘጋጁልን አዲስ የመኖሪያ ቤት አስቀመጡን፤ በእስር ቤት:: አሳሪዎቻችን እኛን በማሰር የተቀጣጠለው የነፃነት ነበልባል ይዳፈናል፤ ፈጥኖም ይጠፋል

ብለው ተስፋ አድርገው ነበር:: ከ «ሳሌም የጠንቋዮች አደን ድራማ» ጋር ብቻ በሚነፃፀር የፖለቲከኞች የሶፕ ኦፔራ የውሸት ክሶች ቁልል ከመሩብን:: ማስረጃ ተብዬዎችን ፈበረኩብን:: «ምሥክሮችን» አሰለጠኑብን:: በተለምዶ የሕግን የበላይነት ያስከብራል ተብሎ የሚታመነው ተቋምም ማናቸውንም ዓይነት ተቃውሞ እና ውልብታውን ለመደፍጠጥ ተሽቀዳደመ::

ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አባላት መሐል ጥቂቶቹ ኃያላን ባሳዩት አማቂ ልፍስፍስነት ሳቢያ ኃይሉን ዳግም ያደሰው አምባገነኑ አገዛዝ የአጨቋቆን ጥበቡን ቀይሮ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ ለመደምሰስ ለፋ::

እርግጥ ነው... ከብረት ዘንግ ኋላ በእስር ቤት መኖር ያማል፣ ያሰቃያል:: ሕመሜን የሚያብሰው የአገሬን ሰዎች ትግል ሳልቀላቀል በልቤ ጆሮዎች ብቻ በማድመጤ ነው:: ሥቃዬን የሚያበረታው ከትግሉ አውድማ በሥፍራ ቅርብ ሳለሁ ያለ ፈቃዴ ርቄ ሳልወድ በግድ በመንፈስ ወኪልነት ብቻ የትግሉ አካል በመሆኔ ነው:: ይሁን እንጂ መከራዬ እዚያው ጋር ይቆማል::

የእኛ መታሰር የነፃነቱን መንፈስ አላጠፋውም:: ይልቁንም ይህንን የነፃነት መንፈስ የታገሉትን በጥላቻ ሞልቶ አንገፍግፏቸዋል:: ክብረ-ቢስም አድርጓቸዋል:: በተለየ አመለካከት ላይ በደረሰው አፈናና ሌሎች የጭቆና ዓይነቶች ሳይበገሩ ብርታትን የተላበሱ ሌሎች ዴሞክራቶች ከልብ በመነጨ ቁርጠኝነት ለነፃነትና ለእኩልነት ተሰለፉ::

እንደምሰማው ከሆነ በነፃ የመናገር የዜግነት መብት ታፍኗል:: ነፃው ፕሬስ ታግዷል:: ነገር ግን የመረጃ መረብ ጆርናሎች እያበቡ ነፃ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩባቸው ጎዳናዎች እየተፈጠሩ ነው:: የግል ነፃነታቸውን እጅጉን የሚወዱ ተሰጥዖ ያላቸው ጸሓፍት በአልፎ ሂያጅ ዘጋቢነት (Blogging) ራሳቸውን ለሳይበር ስፔስ እነሆኝ ብለዋል:: ነፃነትን እና ፍትህን የሚያስሱት ዜጎች በዕምነት የለሾች እና በፍቅር የለሾች ቢንገላቱም፤ ጥቃቱ ብርታትን እና ፅናትን አበራከተ እንጂ አልሸረሸረም:: ይህን የነፃነት እና የፍትህ ጥማት በዓይነ ኅሊናዬ እያሰብኩና እያሰላሰልኩ ታስሬ ባለሁበት በእዚህ የእስር ክፍል እንኳ ምርኮኛ አድርጎኛል::

«ያልኩት ሆነ» ብዬ ቢያስመስልብኝም፤ ትግሉ ከአራት ወራት በፊት ለተናገርኩት «ቅንጅት መንፈስ ነው» ለሚለው መሪ መፈክር እንደ ጉልህ አስረጅ መሆኑ ተረጋግጧል:: ቅንጅት የነፃነት መንፈስ ነው:: ቅንጅት የፍቅር እና የአንድነት መንፈስ ነው:: በምርጫው ክርክሮች ወቅት ይህ መንፈስ የብዙሃንን ሕይወትና አኗኗር ተቆጣጥሯል:: ቅንጅት የዜጎች የተለያዩ ሃሳቦች እና ልምዶች መገናኛ ፎርማታ ሆኖ ነበር:: ሃሳቦቹን እና ልምዶቹን በወል አስተሳስሮ የሚያቀናጅ፣ በውድ የሚያስገድድ የነፃነት ጥልቅ መሻት እና ፍለጋ ነበረው:: በሁሉም የኑሮ እርከን ያሉ፣ ከ«ላፕ ቶፕ» መራቅ ከማይችሉ ባለሙያዎች እስከ የቀን ሠራተኞች፣ ዜጎች መንፈሱ አንድንም ሰው እንኳ ሳያስቀር ሁሉን ነክቷል:: እኛን የሚጠሉን እና አሳሪዎቻችን «ስለምን ተቃዋሚዎችና ሕዝቡ እንዲህ ከልብ ሥር በፈለቀ ስሜት ተገዳደሩን» ብለው ራሳቸውን የሚጠይቁበት ጊዜ መኖር ያለበት ይመስለኛል:: እነርሱም እንደ ሌሎች አምባገነኖች ሁሉ በእርግጥም በጥንቃቄ ራሳቸውን ከእውነቱ ለማሸሽ መጣራቸው አይቀርም:: ይሁን እንጂ እነርሱም እንኳ በመንፈሱ ተፅዕኖ ሥር ወድቀዋል::

በአንድ ጎኑ ቅንጅት የ1980ዎቹን የፖላንድ የአንድነት ንቅናቄን (Polish Solidarity Movement) ይመስላል:: የአንድነት ንቅናቄው ተቃውሞውን የጀመረው በኢኮኖሚያዊ ተሃድሶዎች ጥያቄ ነበር:: ኋላ ላይ ንቅናቄው ቅርፁን ለውጦ ፖላንድን ከራሽያ የእጅ አዙር አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የትግል መሪ ሆነ:: ከምርጫው ክርክሮች በፊት ቅንጅት አንድ አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ነበር:: ቅንጅት አምባገነንነትን አስወጋጅ መንፈስ ወደ መሆን የተሸጋገረው በአስገራሚና ሁሉን በሚያሸንፍ ሁኔታ ተሞልቶ ነው:: ይህ መንፈስ በኢትዮጵያውያን ልብና አዕምሮ ሰርፆ አገሪቱን ያለ ነፃነት መቆጣጠር የማይቻል አድርጓታል::

የቅንጅት መሪዎች በጆን ሎክ አስተምህሮ መሠረት የነፃነት መንፈሱ የበላይ ጠባቂዎች ናቸው:: የእኛ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነት መሠረቱ የውል እና የወኪልነት ተዛምዶ ብቻ ነው:: መታሰራችን ሕዝቡ የሰጠንን ተግባር እንዳንከውን አግዶን ይሆናል:: ነገር ግን የመንፈሱ ሕልውና እና ልዕልና ሕያው ሆኖ ይኖራል::

በ1981 እ.ኤ.አ የጄነራል ወዮች ያርዙልስኪስ መንግስት የፖላንድ የአንድነት ንቅናቄን ለመሰነጣጠቅ እርምጃ ወሰደ:: ንቅናቄውን በ1982 እ.ኤ.አ «በሕግ» አፈረሰው::

*የንቅናቄውን አመራሮች አሰረ፡፡ ነገር ግን ንቅናቄው ሕቡዕ ገብቶ ድርጅታዊ መዋቅሩን ቀጠለ፡፡ በ1989 እ.ኤ.አ የፖላንድ ሕዝብ ንቅናቄውን ያፈረሰውን መንግስት አስገድዶ የአንድነት ንቅናቄው ዳግም ሕጋዊ ሆነ፡፡ ይህን ተከትሎ በተካሄደው የምርጫ ውድድር ንቅናቄው የፓርላማ መቀመጫዎችን በአገሪቱ በሙሉ በዝረራ አሸነፈ፡፡ ይህም የኮሚኒስት ፓርቲውን የአስርት ዓመታት አገዛዝ ፈፀመ፡፡*

*ከዚህ የፖላንድ የአንድነት ንቅናቄ ትይዩ የእኛንም አገርና የቅንጅትን ሁናቴ ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡ እኛ በታሰርን በጥቂት ቀናት ውስጥ የምርጫ ቦርዱ ቅንጅት የሚባል ፓርቲ ሕልውና የለውም ሲል አወጀ፡፡ በልደቱ አያሌውና እና በሪፖርተር ጋዜጣ ርዕሰ-አንቀፅ እገዛ እና አይዞህ ባይነት፤ መንግስት ሕዝቡ የነፃነት ፍለጋ መሻቱን ወደ ጎን ትቶ፤ አትኩሮቱን በአስተዳደራዊ ጉዳዮች (አዲስ አበባን ማን ይረከባታል? በሚል ዘበት) ላይ ለመቸከል በከንቱ ለፋ፡፡ በአዲስ አበባ ያሉ ጥቂት መልካም አሳቢ ዲፕሎማቶች የቅንጅትን ተፈጥሮ እና የሕዝቡን እምቢ-ለነፃነቱ ጥያቄ ባለመገንዘብ በየዋህነት በመንግስት የሴራ ወጥመድ ተጠለፉ፡፡ ኢህአዴግም፣ ልደቱም ሆነ ሪፖርተር ሊረዱት ያልቻሉትና የማያውቁት የትግላችንን ተፈጥሮ ነው፡፡ የእኛ ትግል የነፃነት ትግል ነው፡፡ ሰው ያለ ነፃነቱ ምንድን ነው?*

---

*ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበር ናት፡፡ ይህን ደብዳቤ የላከችው አሁን ካለችበት ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ ቃሊቲ ከሚገኘው ወህኒ ቤት ነው፡፡*